

# ክቡር አምባሳደር አያሌው ማንደፍሮ

ግንቦት 27 ቀን 1927 ዓ.ም እስከ  ሐምሌ 26 ቀን 2011 ዓ.ም

**June 4, 1935 - August 2 2019**

# የአንጋፋው ዲፕሎማት
# የክቡር አምባሳደር አያሌው ማንደፍሮ
## አጭር የሕይወት ታሪክ

አምባሳደር አያሌው ማንደፍሮ ከአባታቸው ከአቶ ማንደፍሮ ኃይለጊዮርጊስ እና ከእናታቸው ከወይዘሮ ዘውዲቱ አየለ ግንቦት 27 ቀን 1927 ዓ.ም (እ.ኤ.አ June 4, 1935) በሐረር ከተማ ተወለዱ።

እድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ በሐረር ከተማ በሚገኘው በራስ መኰንን ትምህርት ቤት ገብተው የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ጨርሰው ፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በአዲስ አበባ በሚገኘው ጀነራል ዊንጌት ትምህርት ቤት አጠናቀቁ። ከዚያም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ በኢንጅነሪንግ ተመረቁ። ለከፍተኛ ትምህርት ወደ አሜሪካን አገር ተልከው ታፍት ዩኒቨርሲቲ ቦስተን ማሳቹሴት (Boston, MA) በኢንተርናሽናል ግንኙነት ዲግሪ ተመርቀዋል።

በ1950 ዓ.ም (እ.ኤ.አ 1958) ወደ እናት አገራቸው ተመልሰው በኢትዮጵያ የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር ውስጥ አሜሪካን ክፍል ተመድበው ሥራ ጀምሩ። በዚህ መሥሪያ ቤት ውስጥ የውጪ ጉዳይ ሚኒስትር የነበሩት የልጅ ሚካኤል እምሩ ልዩ ጸሐፊ ሆነው አገልግለዋል።

ቀጥሎም ክቡር አቶ ከተማ ይፍሩ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሆነው በመሾማቸው ፣ የርሳቸው የቅርብ ረዳትና አማካሪ በመሆን ለዓመታት በሙሉ ታማኝነት ሲሠሩ ቆይተዋል። ከአቶ ከተማ ጋር በነበራቸው ወዳጅነትና የቅርብ ግንኙነት በውጪ ጉዳይ ሚንስቴር ውስጥ ተሰሚነታቸው በጉልህ የሚታይበት ወቅት ነበር።

ስለሆነም ከሚኒስትሩ ጋር በመሆን የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ከመመስረቱ በፊት የአፍሪካ መሪዎችና መንግስታት ለድርጅቱ መመስረት ድጋፋቸውን ለማረጋገጥ በተደረገው የዲፕሎማሲ ጥረት ትልቅ ጉዞ በየዋና ከተሞቹ በማከናወን ውጤታማ አስተዋፅዖ አበርክተዋል። ከክቡር ሚኒስትሩ ጋር በጣምራ አያሌ የአፍሪካ መሪዎች ዘንድ የግርማዊ ጃንሆይን መልዕክቶች በማቅረብና በየግላቸው በማነጋገርና በማግባባት የፈጸሙት ሚና ይታወሳል።

በዚያኑ ዘመን አፍሪካ በካዛብላንካና በሞንሮቪያ ቡድኖች በመከፋፈሏ አዲስ አበባ ላይ ሁሉንም ያካተተ ስብሰባ ለማካሄድ አስቸጋሪ ሆኖ በቀረበበት ወቅት የአቶ አያሌውና ሌሎች የሥራ ባልደረቦቻቸው በዲፕሎማሲው ዘመቻ ታላቁን ድርሻ ይዘው እንደነበር ተነግሯል።



ከዚያም በተጨማሪ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የመመስረቻ ቻርተር በሚዘጋጅበት ጊዜ አምባሳደር አያሌው በማቀነባበርም ሆነ ባበረከቱት ሃሳብ ሥራው እንዲጣደፍ በብዙ ደክመዋል። ስብሰባውም በተከናወነበት ጊዜ ሌት ከቀን ቀልጣፋ በሆነ መንገድ የኮንፈረንሱን ጽ/ቤት ተግባር በሃላፊነት ከፈጸሙት መካከል ስማቸው ሲጠራ ይኖራል።

በናጀር 1955 ዓ.ም (እ.ኤ.አ 1963) ሴኔጋል ፣ ዳካር ከተማ በመጀመሪያው የአፍሪካ የውጪ ጉዳይ ሚኒስትሮች መደበኛ ስብሰባ የደርጅቱ ዋና መቀመጫ የት ከተማ እንዲሆን በሚከራከርበት ጊዜ አቶ አያሌው ከኢትዮጵያውያን መልክተኞች መካከል ንቁህ ተሳታፊ በመሆን ከዳካር ከተማ ይልቅ አዲስ አበባ የድርጅቱ ዋና መቀመጫ ሆና ካይሮ ላይ በ1964 ዓ.ም በተደረገው የመሪዎች ጉባዔ በፀደቀው ውሳኔ ተመርጣለች። ለአገር እድገት ይህን የመሰለ ተግባር ለመፈፀም በመቻላቸው ምንኛ እድለኛ ናቸው ያሰኛል።

በ1957 ዓ.ም (እ.ኤ.አ 1965) አምባሳደር አያሌው ማንደፍሮ መጀመሪያ በረዳት ሚኒስቴርነት ቆየት ብሎ ደግሞ በምክትል ሚኒስትርነት ማዕረግ የአሜሪካንን ክፍል መርተዋል።

በ1963 ዓ.ም (እ.ኤ.አ 1971) የኢትዮጵያ አምባሳደር በመሆን በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ሶማሊያ ተሹመው በሲያድባሬ ዘመነ መንግስት የሁለቱን አገራት ግንኙነት ለማሻሻል ብዙ ጥረት ማድረጋቸው ይታወሳል። ስለሆነም የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገሥት አፄ ኃይለሥላሴ በአምባሳደር አያሌው በተደጋጋሚ በቀረበላቸው ማሳሰቢያ ለመጀመሪያ ጊዜ ሞቃድሾን ጎብኝተዋል። የጉብኝቱ ውጤትም የተመኙትን ያህል ባይሆንም ሁለቱ መሪዎች በቀጥታ መነጋገር መቻላቸው የሁለቱን መንግስታት የአቋም ልዩነት እንደቀነሰው ይገመታል።

በሞቃዲሾ በአምባሳደርነት በቆዩበት ወቅት አምባሳደር አያሌው በሁለቱ አገሮች መካከል የነበረውን ውጥረት በማብረድ ብዙ እንደደከሙና ከጦርነት አፋፍ ሁኔታ ላይ ለመመለስ በብርቱ ጥረዋል።

ከሞቃዲሾ ወደ ሐረርጌ ደጋግመው በመመላለስ ለሶስተኛው ክፍለ ጦር በሚኀበኙበት ጊዜ አምባሳደር አያሌው የሶማሌን መንግስት የመስፋፋት ፖሊሲና የትጥቅና የጦር ዝግጅት ላይ ሙሉ መረጃ በማካፈልና በኢትዮጵያ በኩል ያለውን ጉድለት በግልፅ በመወያየት የሞራል ድጋፍ ለሰራዊቱ እንዳበረከቱ ይታወቃል።

ዓፄ ኃይለስላሴ በተገኙበት የአፍሪካ አንድነት ድርጅት መደበኛ የመሪዎች ጉባዔ በ1965 ዓ.ም (እ.ኤ.አ 1974) በሞቃዲሾ ሲከናወን አጋጣሚውን በመጠቀም የሶማሌው የውጪ ጉዳይ ሚኒስትር ኦማር አርቴ

የድርጅቱ ዋና ጸሐፊ ለመሆን በእጩነት ሲቀርቡ የኢትዮጵያን ድጋፍ እንዳገኙ በማድረግ በማውራቱ የኢትዮጵያ መልዕክተኞች በአንድነት ድርጊቱን በገሃድ አስተባብለው የሰውየው ምኞት ባጭር ሊቀጭ ችሏል። በዚህም ሽኩቻ የአምባሳደር አያሌው ትብብር ከፍ ያለ ነበር።

ከዚያም አከታትሎ የንጉሠ ነገሥቱ መንግስት ሥርዓት በአብዮቱ ሲገረሰስና ደርግ ስልጣኑን በያዘበት ወቅት ለመጀመሪያ ጊዜ መከላከያ ሚኒስትር ሆነው የተሾሙት ሲቪሊያን አምባሳደር አያሌው ማንደፍሮ ነበሩ። የጦር ሰራዊቱ በሞቃዲሾ አምባሳደር በነበሩበት ጊዜ ያሳዩትን ትጋትና የሃገር ፍቅር በመገንዘቡ ለዚህ ሹመት መብቃታቸው ራሱ አስረጂ ነው።



በመከላከያ ሚኒስትርነት ዘመናቸው የሶማሌ የጦር ኃይል ለወረራ መዘጋጀቱን በማወቃቸው ለኢትዮጵያ ጦር መሳሪያ ለማግኘት አያሌ መንግስታት ዘንድ በመልዕክተኝነት ተዘዋውረው ለችግሩ መፍትሄ ለማግኘት በብርቱ ጥረዋል።

በመከላከያ ሚኒስቴር በሥራ ላይ እያሉ ከወይዘሮ ፀዳለ ከበደ ጋር የጋብቻ ሥነ-ሥርዓት ፈጽመው ሁለት ልጆች ፤ ዶክተር ምህረት ማንደፍሮ እና ልጅ ሙሴ ማንደፍሮን አፍርተዋል።






በሱማሊያ ጠረፍ የተከሰተው አስጊ ሁኔታ እየባሰ በሄደበት ወቅት ከምእራብ ዓለም በፖለቲካም በመሳሪያም ድጋፍ ለማግኘት ከተባሉት አገሮች ግንኙነት እንዲሻሻል ምክራቸውን ለደርግ ከመለገስ አልተቆጠቡም። በዚህም ምክንያት ይሆናል ከ30 ወራት ኩርፊያ ቦኃላ የደርግ መንግስት አምባሳደር አያሌውን አምባሳደር በማድረግ ዋሽንግተን የሾመው። ግን ከአሜሪካን ጋር የተቀራረበ ግንኙነት የማይደግፉ ወገኖች አምባሳደሩ አዲስ አበባን በመልቀቂያቸው ዋዜማ የግድያ ሙከራ አድርገውባቸው በተአምር ከአደጋ መዳናቸው እስከዛሬ ሲወራ ቆይቷል።

ዋሽንግተን ገብተው ለጥቂት ወራት ሥራቸውን እንደጀመሩ ከደርግ መንግስት ጋር የነበራቸው ግንኙነት እየሻከረ በመሄዱ በግንቦት ወር 1970 (እ.ኤ.አ June, 1978) ዓ.ም ሥራቸውን የመልቀቅ ውሳኔያቸውን አሳውቀው ተሰናበቱ።

በቨርጂንያ አሌክሳንድሪያ ከተማ በስደት ሲኖሩ ለኤመርሰንና ለኮሞሳት ኩባንያዎች በምክትል ፕሬዝዳንትነት እስከ ጡረታ እድሜያቸው ድረስ አገልግለዋል።

ግንቦት 14 ቀን 1993 ዓ.ም (እ.ኤ.አ May 22, 2011) ሴት ልጃቸው ዶክተር ምህረት ማንደፍሮ በአዲስ አበባ ለአቶ ዘረሰናይ ብርሃኔ ድረው የ3 ልጆች አያት ሆነዋል።



አምባሳደር አያሌው ረቂቅ የሆነ አስደናቂ ባህሪ ነበራቸው በዋሽንግተን ዲሲ በስደት በኖሩበት ወቅት በዳያስፖራው መናኸሪያ ኮከብ እንደነበሩና ሁሉን ሰብሳቢና አያያዥ ሥራቸው እየተነገረ ይዘልቃል። ከዚህም ውስጥ የአፍሪካ ሶሳይቲ መስራች መሆናቸው እንደምሳሌ ሊጠቀስ ይችላል።

አምባሳደር አያሌው ማንደፍሮ በደረሰባቸው የአንድ ሳምንት ሕመም እንደዘውትር ጸሎታቸው ፣ መጨረሻዬን አሳምርልኝ እንዳሉት በፌርፋክስ ሆስፒታል ካለምንም ስቃይ በ84 ዓመታቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል።

በዚህ ከባድ ጊዜ ከአጠገባችን ሆናችሁ

በሃሳብ ላጽናናችሁን ሁሉ

ከልብ እናመሰግናለን።

ቤተሰቦቻቸው

